# አባ መቃርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም ወአውስትራልያ ወዘኵሎን አድያሚሃ
# ABBA MEKARIOS ARCHBISHOP OF THE DIOCESE OF JERUSALEM AND AUSTRALIA

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ሰላምም በምድር ይሁን ሉቃስ 2፤14

ለተወደዳችሁ በአውስትራልያና በመላው ዓለም ለምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን! እንኳን ለጌታችን ለአምላካችንንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት በሰላም አደረሳችሁ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ሰውና እግዚአብሔር የተገናኙበት፤ ትንቢተ ነቢያት የተፈጸመበት፤ እርቅና ሰላም የተሰበከበት ምድራውያንና ሰማያውያን ፍጥረታት በአንድ ላይ እግዚአብሔርን ያመሰገኑበት፤ በዓል ነው።

በዚህ ቀን የሩቅ ምሥራቅ ነገሥታት በኮከብ እየተመሩ በመምጣት ለተወለደው ንጉሥ  ወርቅ ዕጣን ከርቤ እጅ መንሻ አቅርበዋል። ወርቅ ለመንግሥቱ፤ ዕጣን ለክህነቱ፤ ከርቤ ማኅየዊ ለሆነ ሞቱ ምሳሌ እንደሆነ ሊቃውንት ይተረጉማሉ፤፤

የልደትን በዓል ስናከብር ዛሬ ለንጉሡ ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የምናቀርብለት በፊቱ ይዘን የምንቆመው ምን ይሆን? የልባችን ሳጥን በጌታ ፊት ሲከፈት ሊገኝ የሚገባው እንደ ወርቅ የጠራና የነጠረ እምነት፤ እንደ ዕጣን ከሩቅ መዓዛው መንፈስ ቅዱስን የሚስብ የጠነከረ ተስፋ፤ እንደ ከርቤ እስከ ሞት ድረስ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ የጸናና የጨከነ ፍቅር እንጅ ቅንዓትና ምቀኝነት ተንኮልና አድማ ሊሆን አይገባም።

የገና በዓል እረኞች ከመላእክት ጋር የዘመሩበት ለተናቁት ብርሃን የወረደበት በዓል ነው። የገናን በዓል በየቤታችን በተድላና በደስታ ስናከብር የተናቁትንና የተቸገሩትን ወገኖቻችንን ልናስባቸው ይገባል።እኛ ሁሉ ነገር በተሟላበት ቤት ውስጥ ሆነን ስናከብር በዘረኛው የወያኔ መንግሥት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትንና ሜዳ ላይ የወደቁትን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ልናስብና ልንጸልይ አቅማችን በቻለው ሁሉ ልንረዳቸው ይገባል።

ይህንን የነጻነት በዓል በነጻነት ስናከብር ነጻነቱን አጥቶ በእስር ቤት እየተሰቃየ በየአደባባዩ እየተገደለና ከክብሩ እየተዋረደ ያለውን ኢትዮጵያዊውን ወገናችንን እናስታውስ።

በቅርቡ በባህር ዳር ከተማ ዘረኛው የወያኔ መንግሥት ጥምቀተ ባህር አይሸጥም አይለወጥም የታቦት ማረፊያችንንም አሳልፈን አንሰጥም በማለታቸው በአደባባይ በጥይት ለገደላቸው ወጣት ልጆቻችን የኢትዮጵያ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር እረፍተ ነፍስ ይስጥልን። ቤተሰቦቻቸውንም በዚህ የሰላምና የመጽናናት በዓል በቅዱስ መንፈሱ እንዲያጽናናልን እንጸልያለን።በደብረ ማርቆስና በአካባቢው በህጻናት ተማሪዎችና በነዋሪዎች ላይ የሚደርሰው ድብደባና አፈሳ፤ በመፈጸም ላይ ነው

በሌሎች ልዩ ልዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚደርሰው ማፈናቀል ስውር ግድያና እስራት ለሀገራችንና ለቤተክርስቲያናችን በአጠቃላይ ለህዝባችን ታላቅ ሀዘንና ፈተና መሆኑ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም።

በውጭ ሀገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ተባብሮ ሥራ እንዳይሠራና ለወገኑ እንዳይደርስ እርስበርስ በመለያየት እንዲጣላና ሰላም እንዳይኖረው በክፍለ ሀገር፤ በዘርና በጎሳ በመበታተን ቤተክርስቲያኑን እንዳይሠራ ጠንካራ የኢትዮጵያውያን ማኅበር እንዳይኖር አንዱ የአንዱን ስም እንዲያጠፋው የውሸትና የፈጠራ ወሬን በመንዛት በስውር ወኪሎቹ የጥፋት ሥራውን እያከናወነ ይገኛል፤፤

የተደዳችሁ ወገኖቼ

ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከዚህ ዘመን የበለጠ የመከራና የውርደት ዘመን እንደሌለ ለሁላችሁም ግልጥ ነው። የሀገራችን ዳር ድንበርና መሬት የገዳማትና የአድባራት ርስት ለቻይና ለህንድና ለአረብ ነጋዴዎችና ገንዘብ ላለው ሁሉ እየተሸጠና እየተለወጠ ያለበት ዘመን ይህ ዘመን ነው።

# አባ መቃርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም ወአውስትራልያ ወዘኵሎን አድያሚሃ
# ABBA MEKARIOS ARCHBISHOP OF THE DIOCESE OF JERUSALEM AND AUSTRALIA

በኃይላቸው ተመክተው ዓለም አቀፉን ቀኖና ቤተክርስቲያን በመጣስ ፓትርያርካችን በስደት የሚንገላቱበት ዘመን ይህ ዘመን ነው።

ታላቂቱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ኃይሏን ለማዳከም በዘርና በጎሳ የከፋፈሉብን በዚህ ዘመን ነው።ይህንንም በማድረጋቸው የዘረኛው የወያኔ ባለሥልጣናት በአደባባይ የኦርቶዶክስን አከርካሪ ሰብረናል በማለት ሳያፍሩ ፎክረዋል።የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አምላክ ይፍረድ።

የተወደዳችሁ ወገኖቼ!

የልደት በዓል ሰላም በምድር ተብሎ የታወጀበት በዓል ነው። ሁላችሁም በያላችሁበት ለሰላም ተንቀሳቀሱ፤ አብያተክርስቲያናትን አንጹ። ተወያዩ የተጣላችሁም ታረቁ መለያየትን አስወግዱ፤፤ የሚለያዩአችሁንና ለሥራችሁ እንቅፋት የሚሆኗችሁን ሰዎች ገሥጹ ምከሩ፤፤
የተወለደው ንጉሥ የሀገራችንንና የቤተክርስቲያናችንን የመከራ ዘመን ያሳልፍልን።

የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ መላውን ዓለም በበረከትና በሰላም ይጎብኝልን።

አባ መቃርዮስ

የአውስትራልያ እና የኢየሩሳሌም አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ